# አሣ ጎርጓሪ ዘንዶ አወጣ

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ
ግንቦት ፳፻፫ ዓ.ም
nigatuasteraye@gmail.com

የዚህች ጦማር ዋና ዓላማ፡ "ያዲስ አበባው ሲኖዶስ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ከቀሩት አኀት አብያተ ክርስቲያናት ተነጥላ ከሀያ በላይ ስህተት ሰርታለችና ትመርመር የሚል ክስና ወቀሳ አቀረበ" ብሎ ሀራ ዘተዋህዶ ባቀረበው ዜና፤ ግራ የተጋባችሁ ክርስቲያኖች፤ "በአኀት አብያተ ክርስቲያናት ሐዋርያዊ ትውፊት አንጻር እንዴት ትመለከተዋለህ" ብላችሁ ላቀረባችሁልኝ ጥያቄ ለመመለስ ነው።

ይህ የቀረበው ሀሳብ የሀራ ዘተዋህዶ ድረ ገጽ ፈጠራ ከሆነ፡ "አባት ሆ ይ ! እኔ በአንተ አንተ በእኔ እንዳለህ እነርሱም በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ" (ዮሐ 17፡ 21") በሚለው ክርስቶሳዊ ቃል፤ አንድነታቸውን አጽንተው በኖሩት በአኀት አብያተ ክርስቲያናት ላይ እየዘመተ ነው ማለት ይቻላል። ምናልባትም ከጥንት ጀምሮ እነዚህን ጥንታውያት አብያተ ክርስቲያናትን ለማጥፋት የሚታገሉት የሰባልዮስ ወይም የአርዮስ ተከታዮች ሊሆን ስለሚችል የአኀት አብያተ ክርስቲያናት አካላት በመተባበር አወቅንብህ ልንለው ይገባናል።

ሀራ ዘተዋህዶ እንዳለውም፤ ያዲስ አበባው ሲኖዶስ፤ በጥታዊት ኦርቶዶክሳዊት በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ላይ ይህን ክስ አቅርቦት ከሆነ፤ ያዲስ አበባው ሲኖዶስ፡ የግብጽን ቤተ ክርስቲያን የከሰሰባቸውን ነገሮች ለህዝበ ክርስቲያኑ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ይኖርበታል።

ያም ሆነ ይህ ህዝበ ክርስቲያኑን ግራ የሚያጋባ ሀሳብ በሁለቱም ጥንታውያት አብያተ ክርስቲያናት ላይ ሲሰራጭ ፤ ከህዝብ ጥያቄ እስኪመጣ በዝምታ ወይም በምሥጢር መያዝ የለበትም። ይህን የመሰለ ግራ የሚያጋባ ነገር ሲከሰት የኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናትን ትውፊት ባለቀቀ መንገድ የሊቃውንት ጉባዔ ለህዝብ ግልጽ ማድረግ ነበረበት። ባለማድረጉ አሁንም እንደ ቀደመው ዘልቆ ከኛ ላይ ደረሰ።

እኔ ዘንድ ሲደርስ አልሰማሁም አላየሁም ብየ አልዋሽም። አያገባኝም አይመለከተኝም ብየ ራሴን በማግለል ባእድ አላዳርግም። "በእናንተ ስላለ ተስፋችሁ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ስጡ" (2ኛ3፡15) የምትለውን ሀዋርያዊት ትውፊት መሰረት በማድረግ፤ ከግል ጥቅምና ክብር ሳናነካካ፤ እውነቱን በመናገራችን የሚያስከትልብንን ነቀፋና ዘለፋ ሳንሸሽ ለሚቀርብልን ጥያቄ ሁሉ እንድንመልስ ከሊቃውንት አባቶቻችን የተረከብናት አደራ ታስገድደናለች። "ወቃለ እሉ አበው ናነብብ ወተስፋሆሙ ንሴፎ ወዛቲ ሃይማኖት እምነትነ ወትምህርትነ ወተሰፋነ እንተ ባት ነሀዩ ወባቲ ንመውት ወባቲ ንትነሳእ በፈቃዱ

ወበሥምረቱ ለአምላክነ" (ሃ አ 94፡22) ከሚለው ምንባብ እየተነሱ ደጋግመው በአጽንኦ ያስተማሩንን መካድም ነው።

ይህም ማለት፡- አባቶቻችን እንድናስተምራት እንድንኖርባት እንድሞትላትና እኛን ለሚከተሉ ልጆችም በቃላችን በግብራችን እንድናቀብላቸው በትልቅ ተስፋ አስተምረውናል። ለማስረከብ ብቻም ሳይሆን፤ ያለንበትን የመሰለ ግራ የሚያጋባ ዘመን ሲገጥም የተፈጠረውን መለያየት በመጠቀም የግል ጥቅም የሚፈልጉ ሰዎች በህዝቡ መካከል እየገቡ የተዋህዶን እምነት የሚያዛባ ስህተት በድፍረት እንዳይከቱ ለመከላከልም ጭምር ነው።

በሌላ በኩልም፡- ህዝብን ግራ የሚያጋባ ይህን የመሰለ ችግር ሲከሰት አስቿኳይና ትክክለኛ መልስ የሚሰጡ ሰዎች ባሉበት ቦታና ዘመን፤ የኔ ቢጤ ሁሉ ዝም እንድንል ከዚህ በታች የምጠቅሳቸው መምህሮቻችን አስተምረውናል።

ቴወዶስዮስ የሚባለው ኦርቶዶክሳዊው ሊቅ "ወአነ አአምር ርቱዐ ከመ ኢይደሉ ህዝባዊ ይምሀር መምህራነ ወእመ አኮሰ ይመስል ከመ ነዳይ ዘይጸውእ ባዕለ ከመ ይብላእ ኀቤሁ፤ ከማሁ ሕጹጸ አዕምሮ አነ" (ሃ አ 83፡26) አለ። ይህም ማለትም፡- የስነ መለኮት፡ የስነ ጽሁፍና የቅኔ ምንጭ ስለሆነችው አሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለመጻፍ ይቅርና። በሊቃውንቱ ፊት ቆሞ ውርድ ንባብ ለማንበብ መድፈር፤ ለራሱ ምንም የሚቀምሰው ሳይኖረው አቅሙን የማያውቅ ድሀ ብዙ ሀብት ያለውን ልጋብዝህ የሚል ሰው መምሰል ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ "እኔ የምጽፍላችሁ ስለ በደለው ወይም ስለተበደለው ሰው አይደለም። ነገር ግን ለእኛ ምን ያህል ታማኞች እንደ ሆናችሁ በእግዚአብሔር ፊት ራሳችሁን እንድታዩ ነው" (2 ኛ ቆሮ 7፡12) ብሎ እንደተናገረውም አወዛጋቢ ስተት ሲከሰት በቸልታ እንዳይታለፍ ያስገነዝባሉ። ይህም ማለት፡- በተበዳይና በበዳይ መካከል ህሊና ሚያሻክር ነገር ሲከሰት መግለጽ፤ የተበዳደሉ ወገኖች የተጎዳዱበትን ስህተት መርመረው የየራሳቸውን ህሊና ፈትሸው እንዲመዝኑና በእግዚአብሄር

ፊት ነጻ ህሊና እንዲኖራቸው ተስፋ በማድረግ እንጅ የበዳይንና የተበዳይን ሰባዊ ባህርይ ለመንካት አይደለም።
ያብነቱ መምህሮቻችን በ4ኛው ክፍለ ዘመን የነበረውን ዮሐንስ የተባለው ሊቅ የተናገረውንም ይጠቅሳሉ። የሮም ባለስልጣናት አገሩን በወረሩበት ጊዜ፤ ለጥቅም የተሰለፈ ሸውከኛ ነገረ ሰሪ በዛ። ካህናቱ ጸሀፊዎች ሁሉ ለሮም መንግስት ስሜትና ፈቃድ እያታዘዙ ከእውነቱ እየሸሹ ሀሰት አራጋቢወች ሆኑ። ዮሐንስ እጅግ አዘነ። የራሱን ሀለፊነት ለመወጣት ተገደደና የሚቀጥለውን ተናገረ። “ ንህነሰ ወሶበ ርኢናሆሙ ከመ ኢይስምኡ ቃለ መጻህፍት ወኢያስመሩ በጽድቅ ንቤሎሙ ። አኮ በፈቃድነ ዘመጻእነ ኀቤክሙ ወኢፈቀድነ ተዋስኦትክሙ አላ አገበርክሙነ አንትሙ በቃለ ንጉሥ . . . . ” ሃ አ 102፡36 አለ። ይህም ማለት “ከእውነት የራቁ በግላዊ ፈቃደ ሥጋቸው እየተገፉ የገዥዎችን ፈቃድ በሚያሰራጩት ንግግር፤ ከተወሀዶ ሃይማኖት ጋራ የተሳሰረችውን ስሜቴን ስለቀሰቀሰብኝ እንጅ ለግል ጥቅምና ክብር ወይም እሰጥ አገባ በሚል ስሜት ተገፍቼ አይደለም”
ይህን የመሰሉ ግራ የሚያጋቡ ነገሮች በቤተ ክርስቲያን ተከስተው፤ ክርስቲያኖች ግልጽ እንዲሆንላቸው ሲጠይቁ በዝምታ፡ በግዴለሽነትና በምናገባኝ ስሜት ማለፍ ክህደት ነው። እውነቱን የሚመሰክሩ ካሉ ለነሱ ቅድሜያ አለመስጠም ድፍረት ነው። እውነቱን በመናገር የሚያስከትለውን ፈተና ፈርቶ መሸሽም ከክርስትና ተልእኮ ውጭ ነው። በዚህ መንፈስ በመመራት ለጦማሯ መነሻ የሆነውን በሀራ ዘተዋህዶ የቀረበውን ከዚህ በታች አቅርቤ መልሱን ለመመለስ ወደ ዝርዝር ሀተታየ እገባለሁ
ከሐራ ዘተዋህዶ የተወሰደው ሙሉ ሀሳብ
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ እና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎድሮስ፤
“የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ያላትን የሃይማኖት አንድነት ልትመረምር ነው” May 14, 2017
በክርስትናው የነገረ መለኰት እና የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ፣ ከግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋራ፣ የቆየ የታሪክ ግንኙነትና የዶግማ አንድነት ያላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሁለቱ እኅትማማች አብያተ ክርስቲያናት መካከል መታየት ጀምሯል የሚባለው የትምህርተ ሃይማኖት ልዩነት እንዲመረመር፣ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ አዘዘ፡፡
የስብሰባው ምንጮች እንደተናገሩት፣ ምልአተ ጉባኤው ትእዛዙን የሰጠው፣ ምሥጢረ ጥምቀትን በተመለከተ፣ የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣ ሚያዝያ 20 ቀን 2009 ዓ.ም.፣ በካይሮ የተፈራሙትን የጋራ ስምምነት የቅርብ መነሻ በማድረግ በተካሔደ ውይይት ነው፡፡
የካቶሊኩ ፖፕ ፍራንሲስ በቅርቡ ግብጽን በጎበኙበት ወቅት፣ ከኮፕት ቤተ ክርስቲያን ፖፕና የእስክንድርያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ታዎድሮስ ጋራ የተወያዩ ሲሆን፤ ከተፈራረሙት ባለ12 አንቀጾች የጋራ ስምምነት ውስጥ፣ አንዱ የሌላውን ምእመን ጥምቀት ላለመድገም የተስማሙበት አቋም(sharedptism) እንደሚገኝበት ገልጿል፡፡
በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት፣ የሥርዓተ ጥምቀቱ አፈጻጸምና የሃይማኖት ምስክርነቱ፣ መሠረታዊ ልዩነት እንዳለው የገለጹ ምንጮች፤ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን አካሔድ፣ የነገረ መለኰትና የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ባላቸውና ኦሪየንታል ተብለው በሚታወቁት፥ የኢትዮጵያ፣ የሶርያ፣ የአርመንና የሕንድ እኅትማማች አብያተ ክርስቲያናት ቅዱስ ሲኖዶሶች ያልተመከረበት እንደኾነ አስረድተዋል፡፡
በሥርዓተ ጥምቀት ላይ የሚፈጠረው ልዩነት፣ በሌሎቹ የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በሚኖረው አንድነት ላይ ተጽዕኖ እንዳለው ምንጮቹ ጠቅሰው፥ በሥርዓተ ቊርባን፣ ከጥንተ አብሶ አንጻር የድንግል ማርያም ቅድስና፣ የካህናቱ ሥነ ምግባር (ሲጋራ ማጤስ)፣ የመሳሰሉት ኻያ ያህል ልዩነቶች በውይይቱ ወቅት እንደተነሡና ከቀደሙት ታላላቅ አባቶች አስተምህሮ ጋራ ያላቸው መጣጣም ጥያቄ ማሥነሳቱን አመልክተዋል፡፡
ቅዱስ ሲኖዶሱ በየጊዜው በሚያካሒደው ስብሰባ፣ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋራ በትብብር መሥራቱ እንዲጠናከር፣ በተለይም ከግብጽ ኮፕት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ለቆየው ግንኙነት ትኩረት እንዲሰጠው ቢያሳስብም፣ በትምህርተ ሃይማኖት ረገድ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከሚታዩት ተናጠላዊ አካሔዶች አንጻር ዶግማዊና ቀኖናዊ አንድነቱ እንዲመረመር ስምምነት ተደርሶበታል፤ የሊቃውንት ጉባኤውም፣ ልዩነቶቹን አጥንቶ ለቀጣዩ ዓመት የጥቅምት ምልአተ ጉባኤ እንዲያቀርብ መወሰኑን አስታውቀዋል፡፡
ኮፐቶች፣ የጥንቶቹን ደጋግ አባቶች አስተምህሮ ጠብቆ በመሔድ በኩል ችግር እየታየባቸው ነው፡፡ እመቤታችን ጥንተ አብሶ አለባት፤ ይላሉ፤ ከካቶሊኮች ጋራ “ጥምቀትን አንደግምም” ብለው አንዱ ያጠመቀውን ሌላው ላለማጥመቅ ተስማምተዋል፤ የእነቅዱስ አትናቴዎስንና የእነቅዱስ ዲዮስቆሮስን ውግዘት ወዴት አድርገውት ነው?... ቅዱስ ቊርባኑም ከዚኹ ጋራ ተያይዞ የሚታይ ነው፤ ተረፈ መሥዋዕቱን አውጥተው ለሕዝብ ያድሉታል፤ በመንገድ ይሸጡታል፤ በዐውደ ምሕረት ሲጋራ የሚያጤሱ ጳጳሳትን አይተናል፤ ይኼን ፈቅደዋል፤ የመዝሙር ሥርዓታቸው እንደ ፕሮቴስታንቶች በባንድ ነው፤ የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ወዴት ነው እያመራች ያለችው? የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በእኒኽና መሰል ዶግማዊና ቀኖናዊ ልዩነቶች ላይ የተጠና አቋም መያዝ አለባት፡፡ የልዩነት ነጥቦቹ፣ በታመነባቸው የሊቃውንት ኮሚቴና በቋሚ ሲኖዶሱ የቅርብ ክትትል ተጠንተው ለቅዱስ ሲኖዶሱ ውሳኔ ሊቀርብ ይገባል፡፡

በተያያዘ ዜና፣ ምልአተ ጉባኤው፣ ግብጻውያን በፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ በጣልቃ(ሥርዋጽ) የጨመሩት ነው የተባለው አንቀጽ፣ በቀጣይ የመጽሐፉ ኅትመቶች እንዲቀር መወሰኑ ተገልጿል፡፡ "ኢትዮጵያውያን ከሊቃውንቶቻቸው ጳጳስ አይሹሙ" የሚለው ሥርዋጹ፣ በግብጾች እንደሚነገረው፣ በኒቂያ ጉባኤ 42ኛ አንቀጽ ያልተወሰነ፣ የነጻነትን ክብር የሚቀንስ ዘረኛና ሐሰተኛ ቀኖና (pseudo canon) ነው፤ ተብሏል፡፡

በአራተኛው ክፍለ ዘመን፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ጥያቄና ፈቃድ በግብጽ ከተሾመው ቅዱስ ፍሬምናጦስ በኋላ እስከ 1951 ዓ.ም. ይሾሙ የነበሩት ጳጳሳት ግብጻውያን እንደነበሩ ያስታወሱት ምንጮቹ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ከሥራቸው ለማድረግና ጳጳሳትን በሾሙ ቁጥር የኢትዮጵያ ነገሥታት የሚልኩላቸው የወርቅ የብር የዕንቁና የአልማዝ ገጸ በረከት እንዳይቀርባቸው፣ ከአገራቸው ከሊፋዎችና ሡልጣኖች ጋራ መክረው ያስገቡት መኾኑን አስገንዝበዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከራሷ ልጆች የራሷን ፓትርያርክና ጳጳሳት መሾም ከጀመረች ግማሽ ምእት ዓመት በመቆጠሩና አንቀጹም ሐሰተኛ ቀኖና በመኾኑ፣ በቀጣይ ኅትመቶች እንዲቀር ቅዱስ ሲኖዶሱ ወስኗል፡፡

ከዚኹ ሥርዋጽ ጋራ በተመሳሳይ፣ የስንክሳር ሚያዝያ 10 ቀን ንባብ አብሮ ታይቷል፡፡ ጉዳዩ፥ በመንበረ ፕትርክና ራስን የመቻል ጥያቄ ባፈለቀው በቅዱስ ንጉሥ ሐርቤና በጊዜው ግብጻዊ ጳጳስ አባ ሚካኤል

የተፈጠረውን ጠብ መነሻ ያደረገ ነው፡፡ ቅዱስ ንጉሥ ሐርቤ፥ የኢትዮጵያን ስፋት የሕዝቡን ብዛት በማየት፣ ሰባት ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ፣ የጊዜውን ግብጻዊ ጳጳስ አቡነ ሚካኤልንና ሊቀ ጳጳሱን አባ ገብርኤልን ደጋግሞ ጠይቋል፡፡

"ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳት ይሹሙልኝ" ማለቱን እንደ ኃጢአት፤ የግብጹን ሊቀ ጳጳስ አባ ገብርኤልን እንደ ገባሬ ተኣምር በመቁጠር ስሙን እንኳ ሳይጠራ፡- "ንጉሡ፥ ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ በመጠየቁ እግዚአብሔር ተቆጥቶ በአገሩ በኢትዮጵያ ላይ መቅሠፍት አወረደበት፤" ይላል፣ በዘመኑ የወረደውን ድርቅና በሽታ በመጥቀስ፡፡ እግዚአብሔር እንዲኽ ዓይነቱን የተቀደሰ ሐሳብ ይባርካል እንጅ በዚኽ የማይቆጣ መኾኑን፣ ምልአተ ጉባኤው፣ ይህም ንባብ ከስንክሳሩ ቀጣይ ኅትመቶች እንዲወጣ ወስኗል፡፡

በዚህ ዘመን ያለው ሲኖዶስ "የተናጠል ስራ ሰርታለችና ትምርመር" የሚል በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያቀረበውን ክስና ወቀሳ ሐራ ዘተዋህዶ ከዚህ በላይ ባቀረበው ሀሳብ ግራ የተጋባችሁ ክርስቲያኖች፤ "በአኀት አብያተ ክርስቲያናት ሐዋርያዊ ትውፊት አንጻር እንዴት ትመለከተዋለህ" ብላችሁ ላቀረባችሁልኝ ጥያቄ ከዚህ በታች በዘረዘርኳቸው አናቅጽ መመለስ እሞክራለሁ።

1 የእስክንድርያ ፓትርያርክና የሮማው ፖፓ ተፈራረሙ።

2ኛ በጥንተ አብሶ አንጻር

ሀ. ከአምስቱ አኀት አብየተ ክርስቲያናት አንዷ በተናጠል የማትወስናቸው

ለ. ከአምስቱ አኀት አብየተ ክርስቲያናት አንዷ በተናጠል የምትወስናቸው

ሐ. አራት ገጸ ምንባባት

መ. አምስት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በቅኔዎቻቸው የሰጡት ምስክርነት

ሠ . ዶክተር አክሊሉ የሰጡት ምስክርነት

3ኛ. የካህናት ምግባር

4ኛ. ተረፈ መስዋዕት

5ኛ. ይመርመር

1ኛ የእስክንድርያው ፓትርያርክና የሮማው ፖፕ አንዱ የሌላውን ምእመን ጥምቀት ላለመድገም (shared baptism) ተስማምተው ተፈራረሙ።

ይህች አረፍተ ነገር የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መሰረት የሆኑትን ምሥጢረ ስላሴንና የጥምቀቱን ስርአት አካታ የያዘች ናት። ከጥንታዊት ሮማዊት ቤተ ክርስቲያን ጋራ ስላሴ አንድም ሶስትም ናቸው በሚለው በምሥጢረ ሥላሴ ብንስማማም፤ ወደ ውስጥ ስንገባ የኛ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ "ዘሰረጽ እምአብ" （ዮ ሐ 16፡ ） ብሎ የተናገረውን ስትከተል፤ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ግን "ዘሰረጽ እም አብ ወወልድ" በማለቷ እንለያታለን።

ጥምቀትን በተመለከተ ከሮማ ካቶሊክ ጋራ ስለሚኖረን ርቀትም ይሁን ቅርበት ከጥንታውያን ሊቃውንት አንዱ ግራጌታ ወልደ ኢየሱስ የተባሉ ሊቅ፡-

"አይሁድ ግዙራነ አፍአ መቅድመ ኵሉ ግዝሩ እከዮ ለልብክሙ" ብለው የጀመሩትን

. . . . . .

"ቦኑ ታበውሑኑ ከመ ንንግርክሙ

በእንተ ማርቆስ ወንጌላዊ ርእሰ አበዊነ ዘቀዲሙ

ባህቱ አሐተ ነገረ እሴአለክሙ

እመ ትክሉ ተዋሥኦ እምአይቴ ጥምቀትክሙ" （ገጽ 242） ብለው በደመደሙት መወድሳቸው አነጋጋሪ እንደሆነ ነግረውናል። ይሁን እንጅ መንግስት ህዝበ ክርስቲያኑን በመግደል በማሰርና በማሳደድ ላይ ሳለ ይህን የመሳሰሉ ነገሮችን

ለህዝብ ማቅረብ መንግስት የሚፈጽመውን ደባ እንዳናያቸው ለመጋረድ ሆን ተብሎ የቀረበልን ይመስላል።
ሆኖም የግብጹ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና የሮማው ካቶሊክ ፓፓ (shared baptism) በሚል እንዳልተነጋገሩና፤ በዚህ ጉዳይ እንዳልተፈራረሙ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ገልጻለች። "Baptism declaration is only 'documentation for the Pope's visit' ነው ብላለች። (shared baptism) በሚለው ተስማምተው ቢፈራረሙ ኖሮ፤ በምስጢረ ስላሴ ስለምንለያይ ያነጋግር ነበር። ሆኖም "it did not ad any new religious concepts" በማለቷ ከጥንቱ አልጨመረችም አልቀነሰችም። የተፈራረሙት "sought not to repeat baptism" በሚል ነው" በማለት የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ማንም ሳይጠቃት ለህዝቧና ማወቅ ለሚፈልግ ግልጽ አድርጋለች። አሁን ሽኩሙ ያለው ይመርመር እያለ የስሞታ ዋይታ ባቀረበው ባዲስ አበባው ሲኖዶስ ላይ ነው።
የተፈራረሙትንም "ሌላው በጣለው መሰረት ላይ እንዳልገባ ብየ ክርስቶስ ባልተጠራበት ስፍራ ወንጌልን መስበክ የዝወትር ምኞቴ ነው " (ሮሜ 10፡20)። ሲል ቅዱስ ጳውሎስ በተናገረው ብንመለከተው፤ ከሐዋርያዊ ትውፊት ያፈነገጠ አይደለም። ክርስትና ያልተሰበከበት ብዙ አገር እያለ፤ በተሰበከበት አገር ሄዶ በህዝቡ እለታዊ ጥቅም እየገቡ፤ በኦርቶዶክስ የተጠመቀውን ወደ ካቶሊክ በመቀልመም የራስን አድማስ ለማስፋት ላለመሞከር መፈራረማቸው ተገቢነቱ አጠያያቂ አይደለም።
ነጋዴ ሲገናኝ የሚነጋገረው ስለትርፉ፤ ገበሬ ስለምርቱ፡ የፖለቲካ ሰዎችም ከአቻወቻቸው ጋራ ሲነጋገሩ የየራሳቸውን ጥቅም ባማይጎዳ ይልቁንም በሚጠቅም ስምምነት መፈራረማቸው አጠያያቂ እንዳልሆነ፤ የሮማው ፓፓና የግብጹ ፓትርያርክም በተገናኙባት አጋጣሚ ስለሃይይማኖታቸውና ስለ ሰው ልጅ ሁለንተና ተነጋግረው ወደፊት በሰፊው ለመነጋገር በር ከፋች ስምምነት መፈራረማቸው ከሁለቱም የሚጠበቅ ሐዋርያዊ ትውፊት ፈጽመዋልና የሚደገፍ ነው። ሆኖም፤ ያዲስ አበባው ሲኖዶስ በሮማው ፓፓና በግብጹ ፓትርያርክ የተደረገው መፈራረም ይመርመር ብሎ የሰነዘረው አስደንጋጭ ትእዛዝ፤ በራሱ በኢትዮጵያው ሲኖዶስ ላይ ትልቅ ጥያቄ አስነስቷል።
ያዲስ አበባው ሲኖዶስ የግብጽን ቤተ ክርስቲያንን ባላደረገችው ነገር ከመውቀስ ይልቅ፤ በኢትዮጵያ ያለችው የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፤ ስትወገዝበት የነበረችበትን የቅዱስ ዲዮስቆሮስን ቅዳሴ፤ የቅዱስ ያሬድን ማህሌት ከቤተ ክርስቲያናችን በመውሰድና ሰው ሰራሽና ተፈጥሮ ባስከተለው ቀዳዳ እየገባች ህዝቡን ወደ ራሷ መጎተቷን እንድታቆሙ "ሌላው በጣለው መሰረት ላይ እንዳልገባ ብየ ክርስቶስ ባልተጠራበት ስፍራ ወንጌልን መስበክ የዝወትር ምኞቴ ነው "
(ሮሜ 10፡20)። ሲል ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረውን ሐዋርያዊ ትውፊት ተከትለው ለምን አልተፈራረሙም ?
በፊታቸው የሚፈሰው ደም አፈር እንዳይነካቸው ለክብራቸው የተነጠፈላቸው ስጋጃ፤ የሚሰሙት የህዝብ ልቅሶ ሰቆቃውና ዋይታ ለክብራቸው የሚዘመርላቸው የሚመስላቸው ናቸው ባትሉኝም፤ ለአባይ ግድብ ሲባል የወያኔ መንግስት ባዘጋጀው የፖለቲካ ቀመር ወደ ግብጽ ከመሄድ፤ በእምነታቸው ምክንያት ስለተገደሉት ወገኖቻቸው በሀዘን ያሉትን ግብጾችን
ለማጽናናትና ሀዘናቸውን ለመካፈል በቦታው ቀድሞ መገኘት ከሮማው ፓፓ ይልቅ ከእኛ ይጠበቅ አልነበረም ?
ይህን የምለው፡- ለፖለቲካ ሽፋን ልብን ከማማለል በራቀና በእርግጥ ለህዝብ በሚጠቅም መንገድ ስለ አባይ ግድብ ለመነጋገር ወደ ግብጽ መሄድ ተገቢ አይደለም ብየ አይደለም። የሮማው ፓፓና የግብጹ ፓትርያርክ የተገናኙባትን አጋጣሚ በመጠቀም ወደፊት ለሚደረግ ውይይት በር ከፋች ስምምንት እንደተፈራረሙ፤ የኢትዮጵያው ፓትርያርክም
ለአባይ ግድብ ወደ ግብጽ በሄዱ ጊዜ፤ ከሃያ በላይ አሉ ከተባሉት ስህተቶች አንዷን ለምን አላነሱ ? ለምን ዛሬ
ተነሳ ? "አሣ ጎርጓሪ ዘንዶ አወጣ" የሚባለው ይህን ለመሰለ ነገር ይመስለኛል። ወደ 2ኛው አንቀጽ እሻገራለሁ።
2ኛ፡-"ከጥንተ አብሶ አንጻር የድንግል ማርያም ቅድስና፣ የመሳሰሉት ኻያ ያህል ልዩነቶች በውይይቱ ወቅት እንደተነሡና ከቀደሙት ታላላቅ አባቶች አስተምህሮ ጋራ ያላቸው መጣጣም ጥያቄ አስነስቷል" ብሏል።
"ከጥንተ አብሶ አንጻር የድንግል ማርያም ቅድስና ከዚህ ቀደም ተነስቶ ሐዋርያዊ ትውፊቱን በጠበቀ መንገድ ተመርምሮ ለኢትዮጵያ ሲኖዶስና ለሊቃውንት ጉባዔ ቀርቦ ሳለ
ለከፋፋይ ፖለቲካቸው ሲሉ አፍነው ያዙት ። የግል ጥቅም የሚፈልጉ ከሲኖዶሶ እና ከሊቃውንት ጉባዔ ውጭ ያሉ ሰዎች፤ የሚመለከተው አካል እንዲወስን ከመገፋፋት ይልቅ መሰዳደቢያና መከፋፍያ ስላደረጉት፤ ሀዋርያዊት ትውፊትን በመከተል ለአሐት ቤተ ክርስቲያን ቀርቦ ያለቀ መነሳት የሌበት ጉዳይ ነበር።
"ወናሁ ይእዜ ሀለውክሙ በአምጣነ አርድእት። ። እስመ ዘልፈ ትሰምኡ ቃለ ትምህርት ወኮንክሙ ዘከመ ኢሰምአ ግሙራ። ወእመቦ ዘተስእለክሙ እምስእንክሙ አውስኡቶ ዘእንበለ ኅዳጣን እምውስቴትክሙ። ወዘከመዝሰ ዓቢይ ሁጉል ውእቱ"። እንዳለው ሊቁ ማለትም፡-ዘወትር የሚነገረውን ሰምታችሁ የተረዳችሁ ትመስላላችሁ። ዛሬ ተመልሳችሁ ፊደል ቆጣሪወች ሆናችሁ። ጠለቅ ያለ መልስ የሚጠይቅ ነገር ሲነሳ ቀጥ ያለ መልስ መስጠት አልቻላችሁም። በምታሰሙት ጫጫታችሁ ህዝቡን ግራ ከማጋባትና በመካከላችሁ ያሉትን አዋቂወች ማፈናችሁን ትታችሁ መልስ መስጠ ለሚችሉት በሙያው ለደከሙ ሰዎች ልቀቁ። በዚህ ሁኔታችሁ የምትቀጥሉ ከሆነ ግን ጥፋታችሁ እጅግ ይከብዳል"
"የገብያ ግርግር ለቀጣፊ በጀው" እንዲሉ፤ አኀት አብያተ ክርስቲያናት በተናጠል ስለማያደርጓቸውና፤ ስለሚያደርጓቸው ነገሮች ያልተረዱ ሰዎች ቤተ ክርስቲናችንን ከኦርቶዶክስነቷ የሚያወጣ መንገድ እየፈጠሩ የእርስ በርስ መዘላለፊያና፤

የሚጠሉትን ማጥቂያ አደረጉት። ከዚህ በታች እንደተገለጸው ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያናችን ወደ ምትነጻጸርባቸውና ወደምትለካካባቸው ወደ አኀት አብያተ ክርስቲያናት የከንሳስ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አቀረበችው። አሁን ደግሞ እንደገና ተቀስቅሶ ጥያቄ በማስነሳቱ ቤተ ክርስቲያናችን ከአኀት አብያተ ክርስቲያናት ተነጥላ የማትወስናቸውንና የምትወስናቸውን በሀና በለ ከፍየ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ለማቅረብ እሞክራለሁ።

ሀ . ከአምስቱ አኀት አብያተ ክርስቲያናት አንዷ በተናጠል የማትወስናቸው

ኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት አኀት የሚባሉበት ምክንያት በማይለያዩባቸው በተናጠል በማያደርጓቸው ጉዳዮች ነው። በስላሴ፤ በክርስቶስ፤ በእመቤታችን፤ በመላእክት፤ በጻድቃንና በሰማእታት፤ በስርአተ ክህነት፤ በምንኩስና እና በስርአተ ገዳም ላይ ያላቸው እምነት ነው። አሐት የምታደርጋቸውም አውቀው በድፍረት፤ ሳያውቁ በስህተት በማይቀንሱላትና በማይጨምሩባት በሐዋርያዊት ትውፊት ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስ "ኢንተሀብል ናጥብዕ ነሀሊ ርእሰነ ለሊነ ከመ እለ ይንእዱ ርእሶሙ በዘአመከሩ ወአየኑ ለሊሆሙ ወኢያእመሩ ፍካሬሁ ዘለሊሆሙ ይነብቡ. . ዘንበለ መስፈርት" （ቆሮ 2ኛ ቆሮ 10:12_ 14) እንዳለው፡-ይህም ማለት፡-የራሳቸውን መንፈስ እየተከተሉ በራሳቸው ስሜት ራሳቸው በሰሩት መስፈርት አንደሚመሩት አይደለንም። በራሳቸው ህሊና ብቻ የሚመሩ ራሳቸውን ከራሳቸው ጋራ እያነጻጸሩ አያስተውሉም"

አኀት አብያተ ክርስቲያናት በተራራቀ አገር ሲኖሩ አንዷ በተናጠል በስላሴ በክርስቶስ በእመቤታችን በመላእክት በጻድቃንና በሰማእታት በስርአተ ክህነት ምንኩስናና ስርአተ ገዳም ላይ አትጨምርም አትቀንስም። "ተናጸሩ በበይናቲክሙ አሐዱ ምስለ ካልዑ እምውስተ ህዝብክሙ በአበይኖ. . . . እለ በአፍአ ይትኤነኑ"(አ ቅ ገ 216፡ ቁ 8） እንዳለው አትናቴዎስ፤ መንፈሳውያን አገልጋዮች በያሉበት አገር ከመንግስት ወይም ከሌላ በሚደርስባቸው ተጽእኖ ተልእኳቸውን እንዳይስቱ ለቅድስና ለስነ ምግባር ጥራት እርስ በርስ ይጠባበቃሉ። የአምስቱ አኀት አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንቶቻቸው ደግሞ በያሉበት ሆነው በራሳቸው እና ከነሱ ባአንዷ ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ከሌላ የተለየ ነገር እንዳይገባባቸው በተረከቧት ሀዋርያዊት ትውፊት ይለካካሉ።

የአንጾኪያው ሳዊሮስ የተባለው ኦርቶዶክሳዊው ሊቅ የሀዋርያውን ትውፊት መሰረት አድርጎ "ሕሊናነ ባህቲቶ ከመ ኢይትፈጸም ላዕሌነ ቃለ ትንቢት ዘይብል በገስጾ አላ ምሌ ሎሙ ለእለ ይረስዩ ርእሶሙ ባህቲቶሙ ጠቢባነ ፡ አላ እንተሉ እምነተ አቢዊነ ቅዱሳን መምህራነ ቤተ ክርስቲያን እስመ ኵሎሙ ይትአመኑ በመድኃኒነ ከመ ውእቱ ተወከፈ ሥጋ እምህላዌነ （ሃይ 85፡5) በሚለው ትምህርቱ አኀት አብያተ ክርስቲያናትን ከላይ በተገለጹት እምነትና ትምህርት ላይ አንዳች ነገር በተናጠል ሳይጨምሩ ሳይቀንሱ ይመዛዘናሉ ይጠባበቃሉ። በተናጠል ወደ ሚያደርጌቸውና ወደ ማይመዛዘኑባቸው ነገሮች እሻገራለሁ።

ለ. ከአምስቱ አኀት አብየተ ክርስቲያናት አንዷ በተናጠል የምታደርጋቸው

በተዋህዶ ሃይማኖት ከማይመስሏቸው ካካባቢያቸው ህዝብ ጋራ ሲኖሩ፤ መሰረታዊ የተዋህዶ ክርስናቸውን የሚያፋልስ ነገር ሰርጎ እንዳይገባባቸው እየተጠነቀቁ፤ በባህል የሚጠቃለሉ ነገሮች እንደ ምግብ ልብስ ቋንቋና የሚኖሩባቸው መልክአ ምድር በሚፈጥራቸው ተለዋዋጭ ፖለቲካ በመሳሰሉ ጉዳዮች አይተባበሩም። በነዚህ ጉዳዮች ከእርስ በርስ ይገለላሉ።

የቤርስቲያናቸውን ሁለንተና ያላጠኑ ክርስቲያኖች፤ ዘሎ የገባውን ለረዥም ጊዜ ደጋግመው ከሰሙትና የቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንት ጉባዔ ወዲያውኑ ካላስተካከለው ህዝቡ ይቀበለዋል። በነገረ መለኮቱ ጠልቀው ከገቡ ጥቂት ሰዎች በቀር፤ ለንስሀ ለጥምቀትና ለቁርባን ከሚያበቃው ትምህርት ርቀው የነገረ መለኮቱን ጥልቀት በማይረዱት በብዙሀኑ አገልጋዮች ህሊና ሰርጾ ከገባና ከህዝብ ጋራ አብረው ከቆሙ የገባውን የስህተት ትምህርት ማረም ያስቸግራል። ህዝቡን በሊቃውንቱ ላይ ያነሳሱታል። እንዲያውም ለሊቃውንቱ ህልውና አስጊ ሁኔታ ይፈጠራል።

በገጽ ተሰማርተው እለታዊ አገልግሎት ለህዝቡ በመስጠት ላይ ያሉ ብዙዎች ነገረ መለኮቱን ጠልቀው ባይረዱትም መንፈሳውያን ከሆኑ እና ከግል ክብርና ጥቅም የራቁ ከሆኑ፤ ለጊዜው መስሏቸው የሰሙትን መልቀቅ ቢከብዳቸውም፤ የሊቃውንት ጉባዔ የሚወስነውን

ይጠብቃሉ እንጅ፤ ችግር ያስነሳውን ጉዳይ ደፍረው ወደ ህዝብ አያቀርቡትም። የሊቃውንቱ ጉባዔ ጉዳዩ ከቀረበለት በኋላ፤ ባንዳንድ ምክንያት ውሳኔ መስጠት ከተሳነውና ከዘገየ፤ እኛን እንደገጠመን ማለት ነው፤ ወደ አኀት አብያተ ክርስቲያናት ቀርቦ ውሳኔ እንዲሰጥበት ከመገፋፋት አልፈው እርስ በርስ ሊወነጃጀሉበት፤ ሊካሰሱበትና ሊወቃቀሱበት አይገባም" ብለው መምህሮቻችን አስተምረውናል።

ያም ሆነ ይህ፡- እነዚሁ አኀት አብያተ ክርስቲያናት በተናጠል ምንም እንደማይወስኑ መረዳት እንችል ዘንድ አባቶቻችን አንድም እያሉ ያስተማሩባቸውን ቢያንስ 4 ምንባት ለምሳሌ ያህል ከዚህ በታች አቀርባለሁ።

ገጸ ንባባት  የሐዲሳቱ የሊቃውንቱ መጻህፍት መተርጉማን አበው እንዳስተማሩን አሀት አብያተ ክርስቲያናት ተበታትነው በሚኖሩባቸው አገሮች ተወስነው ሳይገናኙ ተለያይተውና ተቆራርጠው በያሉበት ተውጠው እንዲጠፉ በየዘመኑ የተነሱባቸው ኃይላት የሮማ ካቶሊክን ጨምሮ ብዙ ናቸው።

በየቋንቋቸው በሚያቀርቡት ቅዳሴ ከክርስቶስ ጋራ እና ከእርስ በርሳቸው ጋራ አንድ የምታደርጋቸውን ጵርስፎራ ይዘው

“እስመ አንተ ትቤ . . . . ኢይክልዋ አናቅጸ ሲኦል አማስኖታ ወአንቀልቅሎታ” (ቅ ገጽ 100 ቁ 73) እያሉ የሚማጸኑት አምላክ ካንድነታቸው ሳይናወጹ እንዲቆዩ አድርጓቸዋል።

ጌታችን ”እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተ ቅርንጫፎች ናችሁ። ተካዩ አባቴ ነው“ （15፡1__5） እንዳለው አኀት አብያተ ክርስቲያናት በሱ ላይ ያሉ የወይን ሀረጎች ስለሆኑ በያሉበት ሊያጠፋቸው ከሚታገላቸው ምድራውያን ኃይላት ጋራ ለብዙ ዘመን እየታገሉ እስኪመለስ በሀዋርያዊት ትውፊታቸው አንድነታቸውን ጠብቀው ኖረዋል። ይኖራሉ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ “ውስተ እንታክቲ ተተክለት ሐረገ ወይን ወበኀቤነሰ ኮነ አስካለ ጽድቅ እንታክቲ አስረጸት አስካለ ውስተ ምክያድ ወአህዛብ ስትዩ ስቴ ምስጢር” （ሃይ 66፡22） ሲል በተናገረው፤ “በይሁዲ በሂንዱ በቡድሃ በሌላም እምነትና ባህል መካከል የተተከለች የእውነት ፍሬ የምታፈራ ሀረግ የምንረካባት ያንድነት ጽዋችን “ እያሉ አባቶቻችን አስተምረውናል።

ዮሐንስ የሀንስ አፈወርቅ በሌላ ምእራፍ ይህንኑ ሀሳብ ደገመው።

”ወቦቱ አስተጋብአነ እምዝርወት ውስተ እንተ ተዐቢ ሃይማኖት ወረሰየ ሎቱ ህዝበ ጉቡአ ወአቅረበነ ኀቤሁ ለስባሄ “ （ቅዳሴ ገ308 ቁጥ 19） አለ። ይህም ማለት፦በመልክአ

ምድር በባህል በቋንቋና በመሳሰሉት ነገሮች ስንራራቅ በተላቋ ተዋህዶ ሃይማኖት ሰብስቦ ባንዲት እምነትና ስርአተ አምልኮ እንድናመሰግነው ሰበሰቦ አንድ አደረገን።

የአንጾኪው ፊላታወስ፤ የእስክንድራያው አትናቴዎስና አንስጣስዮስ በመልክአ ምድር ተራርቀው ሲኖሩ፤ የሚለያይያነገር በመካከላቸው እንዳይገባ “ንግድፍ ወናርህቅ እማእከሌነ ኩሎ ዘይክህድ ሃይማኖተ ኦርቶዶክሳዊተ ” （ሃ ም 105፡16） ብለው ተመካከሩ። ይህም ማለት፡- በመካከላችን ገብቶ ከኦርቶዶክሳዊት እም ነታችን እንድንርቅና እርስ በርሳችንም እንድንራራቅ ከሚያደርግ ነገር ፈጽመን እንራቅ“ ተባባሉ ።

ያዕቆብ ዘሥሩግ በመልክአ ምድር ተራርቀው ስላሉት አሀት አብያተ ክርስቲያናት አንድነት “በከመ አስተጋባእካ ለዛቲ ህብስት እንዘ ዝሩት ይእቲ ማእከለ አድባር ወአውግር ወውስተ ገዳም ወቆላት ወተጋቢአ ኮነት አሐተ ጽርስፎራ”(ቅ. ገጽ 350. ቁ 68 ) ሲል ተናገረ። ማለትም፡- “ ይህች ጽርስፎራ በሸንተረር በፈረፈር ተዘርተው ከበቀሉ ካደጉ ቅንጣቶች የተገኙ የብዙ ስንዴዎች ስብስብ እንደሆነች፤ እያንዳንዷ እህት ቤተ ክርስቲያንም በያለንበት በቋንቋ በባህልና በመልክአ ምድር ብንለያይም ባንዲት እምነት ባንዲት ጥምቀት ባንዲት ቁርባን አንድ አደረከን።

በአምስቱ አኀት አብያተ ክርስቲያናት ያሉት በያሉበት በየቋንቋቸው በየእለቱ ለቁርባን በሚሰበሰቡበት “ንሁር በፍናዊሆሙ ወንትሉ በአሰሮሙ ንትመሰል ኪያሆሙ ባርክ አባግአ መርዔትከ ወአብዝሀለዛቲ አጸደ ወይን እንተ ተከልካ በየማንከ ቅድስት “ቅዳሴ ስር ገጽ 58፡146__147） እያሉ ይጸልያሉ። ይህም ማለት፡- አሐት (አንዲት) ቤተ ክርስቲያን በሚባሉት በአምስቱ አብያተ ክርስቲያናት አንዲትን የተዋህዶ ኦርቶዶክስ እምነትና ጥምቀት እያስተማሩ ወደ ክርስቶስ የሄዱባትን ሀዋርያዊት ትውፊት እንድንጠብቅ እርዳን።

ከዚህ ቀጥየ አሀት አብያተ ክርስቲያናት የሚለካኩባቸውን መጻህፍት መሰረት በማድረግ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከደረሷቸው ብዙ ቅኔዎች ለምሳሌ ያህል አምስቱን ብቻ ለማቅረብ፤ መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ዝክረ ሊቃውንት በሚል ርእስ ወደ አሳተሙት መጽሀፍ እሻገራለሁ።

ሊቃውንት አባቶቻችን የደረሷቸው ቅኔዎች

ታትመው የቀረቡትን ያንድምታ መጻህፍት ለብቻ በማንበብ ወይም ባጫጭር ኮርሶች የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሊቃውንት አተረጓጎም መረዳት አይቻልም። የስነ መለኮት ንጽጽር (comparative theology) ትምህርት በጥልቀት በሚሰጥባቸው ከፍተኛ ሴሚናሮች መማርን ይጠይቃል። ወይም ቅኔያቸውን ከዘርቅ አላቀው ወደ ስነ ፍጥረትና ወደነገረ መለኮት ካደረሱ መምህራን ጉባዔ መሳተፍ፤ ወይም ከተሳተፉ ሰዎች ጋራ ጊዜ ማጥፋት ይጠይቃል። ስለዚህ ነው ”ቅኔ ያላሸው ቄስ፡ ሙቀጫ ያልፈተገው ገብስ“ አንድ ናቸው

የሚባለው። በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያናችንን የገጠማት ችግር ይህ ይመስለኛል። ከዚህ ቀጥየ አባቶቻችን የደረሷቸውን ቅኔዎች አቀርባለሁ።

መላከ ጸሀይ ተገኘ፡- የተባሉ የደብረ ማርቆሱ ሊቅ

“ቃለ አብ ስብአ እምአመ ኮነ፤ ቅድምና ሥጋሁ ተከስተ መልእልተ ዘታቦር ደብር፤ በሚል የጀመሩትን፡-

”እስመ ዳግሚት ግብጽ ሰማየ ብሄር

በሀጺኖታ አሚነ እመ ብዙሀን አህጉር።

እስመ ዳግሚት ግብጽ ሰማየ ብሔር ” በሚል ደመደሙት። (ዝክረ ሊቃውንት ገጽ 401)

እነህ ሊቅ ቅኔያቸውን የመሰረቱት የአንጾኪያው ዮሐንስ “መሀረነ ዐምድ ጽኑዕ ወማህቶተ ብሩህ ወመምህር ዐቢይ ኦርቶዶክሳዊ አትናቴወስ ዝኩ ዘነበረ ላዕለ መንበረ ማርቆስ ወንጌላዊ ዘትምህርታቲሁ እምስትናፋስ መንፈስቅዱስ ” （ሃ ም 114፡17） ብሎ በተናገረው ላይ ።

አቶ አርአያ ወረታና የተሻ ወርቅ የሚባሉት ሊቃውንት ስለ አሀት አብያተ ክርስቲያናት ሲወያዩ አቶ ወረታ አርአያ ለአቶ የተሻ ወርቅ የገለጹበት
“ዓለመ ፍቅረ ቢጽ እኑዝ ውስተ እደዊሃ” በሚል የጀመሩትን የፈጸሙት
. . . . . . . .. . . . .
“እንዘ ይታራድኡ ተፋቅሮ እብነ ርእሰ ኤርሞን ወሳኔር፤
ለህንጸ ማኅፈድ ማርቆስ ሃይማኖትከ ጠፈር።
ትርጓሜ ወተዋህዶ መሰረታቲሃ ውስተ ደብር” በሚል ነው። (ዝ ገጽ 431) የመሰረቱትም “ይታልው በበይናቲሆሙ በበአሐዱ ተሰናዕው ከመ ውእቱ ወልደ እግዚአብሄር” ብሎ አትናቴወስ በተናገረው ላይ ነው። ሃ ም 24፡ቁ 7
የዲማ ው አለቃ ውድነህ እሸቴ የሚባሉ ሊቅ
“ነሰተ ልዮን በሚል የጀመሩትን ቅኔ የደመደሙት
ሰብአ ሮሜሰ አራሪነ በጽዋእ ክህደት ሰክሩ
ጣእመ ስቴ ወይን ሃይማኖትነ እስከነ ወለጡ ወአምረሩ፤ በሚል ነው። ዝ ገጽ 367 እኒህ ሊቅ ቅኔያቸውን የመሰረቱት የእስክድራያው ዮሐንስ ለአንጾኪያው ኪርያኮስ በላከው መልእክት “ወይትጋደሉ ከመ ይፍልጡ ተዋህዶተ ህላዌያት ወግብራት በአምጣነ ክህደት ወጽርፈት በጦማረ ልዮን ዐላዌ ሕግ （ሃይ 90፡29） ተብሎ በጻፈው ነው።
አለቃ ገብረ ክርስቶስ፡-የተባሉት የአንኮበሩ ሊቅም
አለቃ ኪዳነ ወልድ የተባሉ ሊቅ በቦሩ ሜዳ በኮቶሊኮች የተዘራውን ተንኮል ሳይወላውሉ ጠንክረው በመታገላቸው፤
ጽንዕተ ደብረ ሚካኤል፤ ቦአ ጠቢ ብ ኪዳነ ወልድ አብ ኢያሱ፤
በሚል ጀምረው፡-
“ካልአንሂ አእዱገ ሮም ውስተ ብሔረ ግብጽ ዘጌሠ
በኪዳነ ወልድ ይትከልኡ አድባረ ምድረ ግብጽ ኢያፍልሱ፤
ወአመተቀጸለ ሕገ አክሊለ ሰላማ በርእሱ፤
እምተፈጥሮ አዕዱግ ዘሮምያ አልህምተ ግብጽ ይኄይሱ” （ገጽ 542） በሚል ደመደሙት። ዘሱኑትዩ የተባለው ሊቅ “ወኩሉ ዘይሄሊ በዝንቱ ህሊና ወተሰነአወ ምስለ ዝንቱ ጉባዔ ርኩስ ወአላዊ ህግ ወተዐዳዌ ቃለ ትምህርተ አበው ርቱዐነ ሃይማኖት ” （ሃ አ ም 109፡27） ሲል በተናገረው ላይ መስርተው ነው።
መላከ ኃይል ተድላ፡- የሚባሉትም
“ከንቶ ነገረ እመ ተናገሩ፤ ሰብአ ሮምያ አጽራረ ኢየከውን ለቅያሜ፤ በሚል የጀመሩትን መወድስ፡-
ርኢናሁ ለበትር እንዘ ይጌሰጸ ለሮሜ
ቅሩጸ በንባብ ወጽሩብ በትርጌሜ” ብለው ደመደሙት። （ገጽ 256） ቅኔውን የመሰረቱት ሳዊሮስ የተባለው ሊቅ ”ወናሁ ረከብኩ ኦ እኁው ፍቁር ዘንተ በትረ ጽሩብ ወቅሩጸ በመጻህፍቲከ ወወሀበከ ኪያሁ እሙነ በአምጣነ ክህነት ወአልቦ ዘይረክብ ክብረ “ （ሃይ አበው 87፡7） ብሎ በተናገረው ቃል ላይ ነው።
ሁለት አዛውንት አባቶች ዶክተር አክሊሉ ሀብቴና ደጃዝማች ወልደ ሰማያት በልጅነታቸው የገጠማቸው በዚህ አጋጣሚ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ታሪካዊ ቅርሳችን ነውና ከዚህ በታች አቀርበዋለሁ።
ዶክተር አክሊሉ ሀብቴ የሰጡት ምስክርነት  ዶክተር አክሊሉ ሀብቴ የሰጡትን ታሪካዊ ምስክርነት ግልጽ ለማድረግ፤ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ያደረገቻቸውን አጋጣሚ ባጭሩ መጥቀስ ይኖርብኛል ብየ እገምታለሁ። የጥንተ አብሶ ጉዳይ በከንሳስ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን በተከሰተ ጊዜ፤ በሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ሊቀመንበርነት ይመራ ለነበረው ማህበረ ለካ ህናት ጉባዔ ቀርቦ እንዲጠና አቡነ ይስሀቅ ጠየቁ።
ከህዳር 10 እስከ 16 ቀን 1997 በዋሽንግተን ርእሰ አድባራት ጉባዔው በተካሄደበት ጊዜ በአቡነ ይስሀቅና በሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ጥያቄ ዶክተር አክሊሉ የአቡነ ጳውሎስን መጽሐፍ ወደ አማረኛ ተርጉመው እንዲያቀርቡ ተደረገ። አቡነ ጳውሎስ የጻፉትም ከአኀት አብያተ ክርስቲያናት የኛ ሊቃውንት አበው ከሚያምኑበትና ከሚያስተምሩት ያልተለየ ትክክለኛ አርቶዶክስ ሆኖ ተገኘ።
የከንሳስ ኪደነ ምህረት ሰዎች እምነትና አቋም ከኦርቶዶክሱ እምነትና ትምህርት ጨርሶ የለቀቀ በሂንዱ reincarnation እምነትና በሮማ ካቶሊክ Immaculat conception እምነት መካከል በመዋዡቅ ላይ እንዳለ ተረጋገጠ። ዶክተር አክሊሉም ከዚህ የሚቀጥለውን ተናገሩ።
“እኔና ደጃዝማች ወልደ ሰማእት በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ስንማር፤ አስተማሪዎቻችን ከአውሮፓ የመጡ የሮማ ካቶሊክ መነኩሴዎች ነበሩ። አሁን አቡነ ጳውሎስ የሚያተራምሱበትን ትምህርት በትንሽ መጽሀፍ ቅጽ አባዝተው አደሉን። መጽሀፉን ወደ ቤታችን ይዘነው ሄደንና ወላጆቻችን አዩት። ወላጆቻችንም “ያባቶቻችን ደም ሳይደርቅ ካቶሊኮች በጦርነት ያቃታቸውን ያስኬላ ትምርት እናስተምራለን ብለው ገብተው በተዘዋዋሪ መንገድ የልጆቻችንን አዕምሮ ሊይዙት ነውና ልጆቻችንን ወደዚህ ትምህላርት ቤት አንልክም’ ብለው አመጹ። ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ በትምህርት ግቢ ተገኝተው፤

“እንዲያስተምሩልን ያመጣናቸው ያስኳላውን ትምህርት እንጅ የነሱን ሃይማኖት አይደለም። ሃይማኖታቸውን ማስራጨታቸውን እንዲያቆሙ እናደርጋለን። ልጆቹ ወደ ትምህርት ገበታቸው ተመልሰው ያስኳላውን ትምህርት ይቀጥሉ። መምህራኑን ብናባርራቸው አስተማሪ ስለማናገኝ የምንጎዳው እኛ ነን” በማለት ወላጆቻችንንም ተማሪዎችንም አረጋግተው ወደ ትምህርት ገበታችን ተመለስን ካሉ በኋላ፤ ንግግራቸው በመቀጠል፡- በብስጭትና በሀዘን “በአቶ መለሰና በአባ ጳውሎስ ላይ የኢትዮጵያ አምላክ ይፍረድባቸው። መለሰ ቤተ መንግስቱን ከተቆጣጠረ በኋላ ለኦሮሞች የላቲንን ፊደል በማቀበል በጥላቻ መርዞ የመገንጠልን መንፈስ ዘራባቸው። አባ ጳውሎስ ደግሞ ለዲግሪያቸው ባቀረቡት መጻፍ የኦርቶዶክሱን እምነትና ትምህርት ከመሰከሩ በኋላ፤ ቤተ ክርስቲያናችንን ከኦርቶዶክስ ገንጥለው ወደ ሮማ ካቶሊክ እምነት ከተቷት ! የኢትዮጵያ አምላክ በሁለቱም ይፍረድባቸው ! ብለው፡- ያቡነ ጳውሎስን ፎቶ በእጃቸው ከያዙት መጽሀፍ ገንጥለው ቀዳደው ጣሉት። ደክተር አክሊሉና ደጃዝማች ወልደ ሰማእትም በህይወታቸው ከገጠሟቸው ብዙ ነገሮች ለትውልዱ ሊመሰክሩት የሚገባ የሽምግልና ተልእኮና ስነ ተግባር ነውና ሊሚሰክሩት ይችላሉ። ከዚህ ቀጥየ ”የግብጽ ካህናት ሲጋራ በማጤሳቸው ከአባቶች አስተምህሮ ጋራ ያላቸው መጣጣም ይመርመር“ ወደሚለው አንቀጽ እሄዳለሁ።

3ኛ “የካህናቱ ሥነ ምግባር (ሲጋራ ማጤስ)፣ የመሳሰሉት ኻያ ያህል ልዩነቶች በውይይቱ ወቅት እንደተነሡና ከቀደሙትታላላቅ አባቶች አስተምህሮ ጋራ ያላቸው መጣጣም ጥያቄ ማሥነሳቱን አመልክተዋል” ቤተክርስቲያናችን ሲጋራ ማጤስን አትደግፍም። ግብጾች ቢያጤሱ ከሃይማኖት አንድነታቸው የሚለያቸው አይደለም። ሲጋራ ብቻ አይደለም። ግብጾች እኛ የማንመገባቸውን ይመገባሉ። ቤተ ክርስቲያናችን የራሷ ሰዎች አሳማ እንዲበሉ አታደፋፍርም። ግብጾች ስለተመገቡት ልንነቅፏቸው ተገቢ አይደለም። የቀደሙ አባቶቻችን እንድንነቅፋቸው የነገሩን ከተዋህዶ እምነት ስርአተ ክህነትና ገዳም ተለይተው ሲገኙ ብቻ ነው።አባቶቻችን በምግባቸው በቋንቋቸው አልነቀፏቸውም። እኛንም እንድንነቅፋቸው አላስተማሩንም።

ይልቁንም በስላሴ፤ በክርስቶስ፤ በእመቤታችን፤ በጻድቃን በሰማእታትና በመላእክት ያለንን አንድ የሆንበት እምነትና ትምህርት ከሚያናጋ በቀር በባህላን እንዳንነቃቀፍ የቅዱስ ጳውሎስን ትውፊት አብራርተው አባቶቻችን አስተምረውናል።

ቅዱስ ጳውሎስ “ላንተ ያለህ እምነት በእግዚአብሄር ፊት ለራስህ ይሁንልህ” ሮሜ 14፡ 22 ። ባለው መሰረት፡ ብብሉያቱ ያልተፈቀዱትን የእንስሳት ሥጋ አለመመገብ ለኛ ተስማምቶናል። ለሚመገቡት ግን ከተስማማቸው ይሁንላቸው ከማለት አልፈን፤ ባህላቸው የሚፈቅድላቸው ሰዎች ሲመገቡ ብናያቸው መንቀፍ ስህተት ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ “ርኩስ እንደሆነ ለሚቆጥር ለርሱ ርኩስ ነው“ሮሜ 14; 14 ። እንዳለውም፡- ሲጋራ ማጤስም ሆነ አሳማ መብላት፤ ርኩስ እንደሆነ ለምናስበው ለኛ ለተዋህዶ እምነት ተከታዮች አይስማማንም፤ የራስህ ወገንም ስልጣኔ መስሎት ተስቦ በመግባት እራሱን እንዳይጎዳ የመምከር ሀላፊነትና ግዴታ አለብን። ከራስህ ባህል ውጭ የሆነ ሰው ሲጋራ ሲያጤስና አሳማ ሲመገብ ብታየው መንቀፍ አጸያፊ ነው።

ይልቁንም ቅዱስ ጳውሎስ ላም የሚቆምበትን እርስበርስ የምንተናነጽበት እንከተል። በሙብል ምክንያት የእግዚ ስራ አታፍርስ” （ሮሜ 14:19 20 ） ባለው መሰረት አኅት አብያተ ክርስቲያናት እርስ በርስ የሚመዛዘኑበት የሚተናነጹበትና የሚጠባበቁበት በስላሴ በክርስቶስ በእመቤታችን በጻድቃን በሰማእታት በመላእክት በስርአተ ክህነት በስርአተ ገዳም ብቻ ነው።

በኢትዮጵያ ምድር ሲታሰብ የሚዘገንነውን አህያ ለማረድ ቁራ ሲዘጋጅ፤ ህዝቡ የተቃውሞ ድምጹን ሲያሰማ ትንፋሽ ያላሰማው ሲኖዶስ ሲጋራ አጤሰዋልን ይመርመሩ እያለ ከአድማስ ባሻገር ያሉትን ግብጾች መክሰስ ”ክርስቶስ የሞተለትን በሙብልህ አታጥፋው” （ሮሜ 14:15） ከሚለው ክርስትና ውጭ ነው።

በእምነት የሚመስሉን ግብጾችን ህንዶችና አርመኖች በመንፈሳውያን ነገሮች እንጅ በምግባቸው በልብሳቸው በቋንቋ በመዝሙራቸው ስለማይመስሉን፤ ያንተን ከነሱ ባታገኘው በኦርቶዶክሳዊት እምነታቸው ላይ ጥያቄ ማንሳት ክርስትናና አለመረዳት ነው። ግብጻውን ሲጋራ አጢሰዋልን ይመርመሩ የሚሉ ሰዎች ቤተ ክርስቲያናችንን ያውቋታል ብሎ ለመናገር የሚያሳፍር ነው።

ግብጾች ሲጋራ አጤሱ እያሉ የሚከሱት የሚነጋገሩበት ቁም ነገር በኢትዮጵ ምድር ጠፍቶ እንደ ትልቅ አስቸኳይና መታለፍ የሌለበት አድርገው ይህን ማንሳታቸውስ ተመልካቹን እንዲጠይቅ አያደርገውም ? ይህን በማንሳታቸው በነሱ በራሳቸው ላይ ያስከተለባቸው እንመልከተው።

የሰውን ህሊና ለሱስ ተገዥ የሚያደርጉ እንደ ሲጋራ፤ እጸፋርስ ጫት የመሳሰሉ እጸዋት መጠቀም እንደሌለብን “ወበቁላትኒ ቀታልያን እለ ያማስንዎ ለልብ። ወለኩሉ ዘሥጋ በበሊኦቱ” (ፍ. ነ. አ. 23፡ 51__53 ） በሚለው ምንባብ ላይ በተመሰረተው ሀተታቸው አባቶቻችን የሚከተለውን አስተምረውን ነበር። ህዝባችን እነዚህ ከመሳሰሉ ጎጅ ልምዶች ገብቶ በአካል በመንፈስ እንዳይጎዳ እንድናስተምር ታዝዘናል። ድሮ በህዝበ ክርስቲያኑ ሲሰማ ይዘገንን የነበረ ጫትና ድራግ ከትግራይ ምድር በቀር በመላ ኢትዮጵያ ባህል ሆኗል ይባላል። በዘመናችን ያለው ሲኖዶስ ርቆና አድማስ ተሻግሮ ባህላቸው ያደረጉትን ግብጻውያንን ከመንቀፍ ይልቅ፤ በመሀል አገር የተወለደው ወጣት የሱስ ተገዥ እንዲሆን ካደረገው

ከዚህ መንግስት ጋራ ተስማምተው ለምን ዝም አሉ ?
ጳጳስ ቆሞስ መነኩሴ ሰባኪ ነኝ በሚሉ ሰዎች ህዝባችን በውስጥም በውጭም እየታመሰ በያለበት ወቅት፤ የራሱን ትዳር አፍርሶ ለሰው ትዳር መፍረስ ምክንያት ሆነ እየተባለ ህዝቡ የሚከሰውን ሰው ቆሞስ አደረጉ የሚባሉት አባ ፋኑኤል የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ አካል ናቸው ሊሉ ነው ? በኢትዮጵያ በኤሮፕ ባሜሪካ ያለው ህዝብ በዝሙት በዘረፋ በስርቆት በሀሰት አሰለቹን እያለ የሚከሰው የግብጾችን መነኮሳትና ጳጳሳት ነው ? ለሊቃውንቱ በችሎታቸው በረዥም አገልግሎታቸው ይሰጡ የነበሩትን የማእረግ ስሞች ተላብሰው የኛን ህዝብ በማመስ ላይ ያሉት የግብጽ ካህናት ናቸው ? ይህን ሁሉ ጉድ አቅፎ የያዘ ሲኖዶስ የግብጽ ካህናት ስርአት ለቀቁ በማለቱ "አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ አወጣ" እያልኩ ስለተረፈ መስዋዕት እናገራለሁ።
4ኛ "ግብጾች ተረፈ መሥዋዕቱን አውጥተው ለሕዝብ ያድሉታል" ይህ አባባላቸው ስለ ተረፈ መስዋዕት ምንም ግንዛቤ የሌላቸው አስመስሏቸዋል።
ተረፈ መስዋዕት ከግብጾች ይልቅ በኛ ቤተ ክርስቲያን በሰፊው ይሰራል። ተረፈ መስዋዕት የተባለበትም ምክንያት ለቁርባን ከሚሰየመው የተለየ ህብስት በመሆኑ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን በበቂ ምክንያት የሰራችውን እየጠቀሱ ህዝብ ያላሰበውን ለማደናገሪያ ማቅረብ ጸያፍ ከማለው ቃል ውጭ የሚገልጸው ሌላ ቃል ያለ አይመስለኝም።
"ወኢተመጠዎ እምቁርባን ይሰደድ እምቤተ ክርስቲያን" የሚለው መጽሀፍ በእኛችን እንዳለ በግብጾችም አለ። ይህም የማይቆርብ ከቤተ ክርስቲያን ይውጣ ማለት ነው። በዚህ ክርስቲያናዊ ትውፊት በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ያስቀደሱ ሁሉ ይቆርባሉ። ስለሚቆርቡም በትርፍ የተሰራውን ለበረከት ይሳተፉታል። በኛ ግን ያስቀደሰ ሁሉ አይቆርብም። በዚህ ምክንያት የተረፈውን ሁሉም አይሳተፈውም።
ይህ ዛሬ ግብጾች የተከሰሱበት ተረፈ መስዋዕት፤ አቡነ ቴዎፍሎስ ከተገደሉባቸው የሀሰት ክሶች አንዱ ነበር። በዚያ ዘመን ግብጾች በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በየሳምንቱ ቅዳሜ ተፈቅዶላቸው ይቀድሱ ነበር። ከሳምንታት አንድ ቅዳሚ አቡነ ቴዎፍሎስ የግብጾችን ቅዳሴ ተሳተፉ። ግብጾች በስርአታቸው የቁርባኑ ተሳትፎ ካለቀ በኋላ ተረፈ መስዋዕቱን በአገልግሎት ቅድምና ባለው አረጋዊ አባት እጅ "ዘትሁብ በረከተ ለአግብርቲከ ለእለ ይፈርሁ ስመከ ቅዱሰ" እያሉ ይሳተፉታል። ግብጾች በአቡነ ቴዎፍሎስ እጅ ተረፈ መስዋዕቱን ለመሳተፍ ፈልገው፤ እንዲያሳትፏቸው ጠየቋቸው። እኛ ህዝባችን ሁሉም ቆራቢ ባለመሆኑ ባናደርገውም መጽሐፈ ቅዳሴያችን (ቅ ሐ ገጽ 224 ቁጥ 167) ላይ ስላለ፤ አቡነ ቴዎፍሎስ አስቀድሰው ለቆረቡት ግብጻውያን አሳተፉ።
በጊዜአዊ ተሀድሶ ጉባዔ ስም በዶክተር ክነፈርግብ ዘለቀ ይመራው ለነበረው ስብሰብ ተላላኪ የነበረ ሰው (በስም ቁስ) እንደ አጋጣሚ አይቷቸው ኖሮ፤ በአቡነ ቴዎፍሎስ ላይ የሀሰት ክስ ይሰበስብ ለነበረው ለነደክተር ክነፈ ርግብ ዘለቀ ጊዜአዊ ተሀድሶ ጉባዔ "አቡነ ቴዎፍሎስ ቁርባኑን ለህዝብ በማደል አረከሱት" ብሎ አቀበለ። አቡነ ቴዎፍሎስን ለመግደል ምክንያት ይፈልጉ የነበሩት እነ ዶክተር ክነፈርግብ ዘለቀ አቡነ ቴዎፍሎስን እንዲገደሉ ካደረገባቸው ወንጀሎች አንዱ ይህ ነበር። በደርግ ጊዜ አቡነ ቴዎፍሎስን ያስገደሉ ሰዎች ባለመቀጣታቸው፤ በአቡነ ቴዎፍሎስ ላይ የተፈጸመው በደል፤ አድማስ በመሻገር በደርግ ዘመን ከነበረው ደባ እጅግ ከፍቶና ሰፍቶ በራሷ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ላይ መጣ እያልኩ "ኢትዮጵያውያን ከራሳቸው ሰው ጳጳሳት አይሹሙ ብለው ግብጻውያን በመጽሀፉ መከተታቸው ዘረኝነት ነውና ይታረም" ወደሚለው እሄዳለሁ።
5ኛ በፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ በጣልቃ(ሥርዋጽ) ኢትዮጵያውያን ሊቃውንቶቻቸው ጳጳስ አይሾሙ" የሚለው በኒቂያ ጉባኤ 42ኛ አንቀጽ ያልተወሰነ፣ የነጻነትን ክብር የሚቀንስ ዘረኛና ሐሰተኛ ቀኖና ነውና ይታረም።
"ኢትዮጵያውያን ሊቃውንቶቻቸው ጳጳስ አይሾሙ" የሚለው መታረሙ የሚደገፍ ቢሆንም፤ የቀደሙ አባቶቻችን ከጣሊያን ጋራ ሲተናነቁ ለነጻነት ሲታገሉ ለተዋህዶው እምነት ሲጠነቀቁ ህይወታቸውን የሰጡትን አቡነ ባስልዮስን የመጀመሪው ፓትርያርክ አርገው በሰየሙ ጊዜ በግብር ሽረውታል።
መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ በ1938 ዓ/ ም በደረሱት ቅኔ
"እስራኤል እምግብጽ አመ ይወጽዑ ብለው ጀመሩትን መወድስ
. . . . . . . . .
አመስ አውጻእከነ ገብረ ጊዮርጊስ አቡነ እምቅንየተ ግብጽ ከማሆሙ
. . . . .
ሐልዮ ሚጠት መንገለ ግብጽ አምጣነ አልቦ ኀቤሆሙ" ዝ ገ 243 ብለው በመደምደም ነግረውናል በታሪክም መዝግበውልናል።
በዚህ ዘመን እንደተደረገ ለማስመሰል "የነጻነትን ክብር የሚቀንስ ዘረኛና ሐሰተኛ ቀኖና ነው" እያሉ የግብጽን ቤተ ክርስቲያን መዝለፍ፤ አሁን በዘመናችን በአገራችን በህዝባችን ላይ የሚደረገውን "የነጻነትን ክብር ቅነሳ፤ ዘረኛና ሐሰተኛ ቀኖና" ለመሸፈን ሆን ተብሎ የተደረገ አስመስሎታል።
ታርሞ የማያልቅ ግፍና ደባ የማይደረገብት ዘመን ቢሆን፤ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና አማራውን ሰበርኩት የሚል

መንግስት ያልነበረበት ዘመን ቢሆን ሀሳቡ ተቀባይነት ይኖረው ነበር። ቤተ ክርስቲያንና አማራውን እየሰበረ ነገድን ከነገድ ጋራ የሚያጋጭ የሚያጋድል እና የሚገድል መንግስት፤ አትስበረኝ አትግደለኝ አትዝረፈኝ ማለት መታረም ያለበት ስርአት አልበኝነት ነው እያለ ህዝቡን የሚያሰቃይ መንግስት ባለበት ዘመን፤ አባቶቻችን ያስወግዱትን የግብጾችን ስህተት እያነሱ፤ አሁን ባለንበት ዘመን የግብጾች ክርስቲያኖች የኛን ክብር እንዳዋረዱና በዘረኝነት እንደከፋፈሉን አርነ ይታረሙ ማለት ከትልቅ ትዝብት ላይ መውደቅ ነው። ስህተትን ለማረም ወይም ይታረም ለማለት ብቃት ያለው ድርጅት ወይም ግለ ሰብ የለም። ካለ ደግሞ ያ ሰው ወይም ድርጅት ቅዱስ ነው። ለዚህ ቅድስና ምሳሌ ሆኖ መገኘት የሚገባው ቅዱስ የሚለውን ቅጽል የተሸከመ ሲኖዶስ ነው። ከነአባ ፋኑኤል ቢጤዎች ክምች ትዳር ያፈረሰና የሰው ትዳር የሚፈርስ ቆሞስ ከመፈልፈል

በቀር ምን አይነት እርማት ይመነጫል ?

ሰሞኑን Margret J. Wheatley የሚባሉ { Leadership and the new science } በሚል ርእስ ያሳተሙትን መጽሀፍ አነብ ነበር ። በ ገጽ 7 ላይ "As Enstein is often quoted as saying: No proplem can be solved from the same consciousness that ceated it." ብለው የጠቀሱት ስለዘመናችን ሲኖዶስ የሚናገሩ መሰለኝ። "ችግር በሚፈጥር ጭንቅላት ችግር አይፈታም" ሲል አንስታይን ተነገራት ብለው የጠቀሷት አረፍተ ነገር እንደ ክብሪት በጭንቅላቴ ተጫረች። "ከፉ ሰው የከፋት ምንጭ ከሆነው ልቡ ክፋትን ያመነጫል"(ማቴ 12፡35 ) ብሎ ጌታችን ቀድሞ የተናገረውን አንስታይን

ሲያረጋግጠው፤ ለምን በዚህ ዘመን ተፈጠርኩ ከማለት ሌላ ምን ይባላል ?

በቤተ ክርስቲያናችን በቅርቡ በዘመናችው የተከሰተውን ልጥቀሰው። ከአቡነ ጳውሎስ እረፍት በኋላ፤ "እርቁ ሳይፈጸም ፓትርያርክ አይመረጥ ይመረጥ" የሚል ክርክር በተነሳ ጊዜ፤ በዘመናችን አሉ ከሚባሉት መምህሮቻችን አንዱ በጀርመን የሚኖሩት ሊቀ ካህናት ዶክተር መራዊ ተበጂ "የተጀመረው እርቅ ሳይቋጭ ምርጫው መጀመር አይገባም" አሉ።

ያዲስ አበባውን ሲኖዶስ እንመራለን ከሚሉት አንዱ፤ የምሁሩን ቀኖናዊ ተግሳጽና ምክር ተቀበልው ስህተቱን ለማስተካከል እንደ መሞከር፤ "ከአምስት ወደ ስድስት እንሻገራለን እንጅ ከአምስት ወደ አራት አንመለስም" ሲሉ ነገረ ዘርቅ አስተጋቡ።

ሊቀ ካህናት መርዓዊ፤ ጎርጎርዮስ የተባለው ሊቅ በዘመኑ ከእውነት እያፈነገጡ ቤተ ክርስቲያንን ይበጠብጡ ለነበሩ አብያጽ ሀሳውያን "ወሶበሂ ንኤብስ ኢናጽንእ ልበነ አላ ንትመየጥ ፍጡነ ለንስሀ" (ሃ አ ም 37፡2) ብሎ የተናገረውን በመንተራስ፤ ቀኖናዋንና ነገረ መለኮቱን እየተማሩ ያደጉት በመሆናቸው "ስህተትን የማስተካከል እንጅ የቁጥር ቀኖና የለንም" ሲሉ ያስተላለፉት ተግሳጽ ሲኖዶሱ የሚጥስ አለመሰለንም ነበር።

እኔም በዚያ ወቅት "ከአምስት ወደ ስድስት እንሻገራለን እንጅ ከአምስት ወደ አራት አንመለስም" የሚለውን ነገረ ዝርቅ ነቅፌ፤ የዶክተር መራዊን ቀኖናዊ ሀሳብ ደግፌ በዚህ ግርግር ፓትርያርክ መሰየም ቤተ ክርስቲያናችን አትቀበለውም። እንዲያውም "ምቱር" ትለዋለች ብየ የቤተ ክርስቲያናችንን ቀኖና ማቅረቤን አስታውሳለሁ። የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ጥረት ተቀባይነት ሳያገኝ፤ "ከምርጫው በፊት እርቁ ይፈጸም የሚሉ ይገደሉ" የሚሉት የነአቶ ስብሀት ነጋ ሀሳብ ተቀባይነት ኖሮት ምርጫው ተፈጸመ።

ታዲያ ዘርቀኛና አዳዲስ ተክሎችን ያቀፈ፤ የሚሰራው በዘረኝነትና በጉቦ፤ የጵጵስናውን ሹመት የሚያድለውም በመንፈሳዊ ብቃት ሳይሆን በኮታ ነው እየተባለ በመከሰስ ላይ ያለው ያዲስ አበባው ሲኖዶስ፤ አገር የሚያጠፋ የባሰ አርም በቤተ ክርስቲያናችን ሊከመር ካልሆነ በቀር ምን ብቃት ኖሮት ነው መጽሐፍ የሚያርመው? ዛሬ ይህ መንግስት በሰበከው ዘረኛነት በአገራችን በደብራችን መኖር አቃተን መሔጃ አጣን እያለ ህዝባችን በሚላቀስበት ጊዜ፤ እኛ ከመፈጠራችን በፊት የነበረውን እየጠቀሱ "ግብጻውያን ዘረኞች ናቸውና ይታረሙ ማለት" አሳ ለማውጣት ሲጎረጉር፤ ዘንዶ የጎተተውን ሰው

መምሰል አይሆንምን ? ከዚህ በላይ በገለጽኳቸው አንቀጾች ከህንድ ከአርመንና ከሶርያ ተለይቶ በተናጠል በመሄድ ላይ ያለውና ወደ ሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በማዘንበል ላይ ያለው በዚህ ዘመን ያለው ሲኖዶስ እንደሆነ በመጠኑ ያሳየሁ ይመስለኛል።

በተረፈ፡- ሀራ ዘተዋህዶ ባቀረበው ዜና ግራ ተጋብታችሁ "አንተ ምንትላለህ ? ብላችሁ የጠቃችሁኝ ክርስቲያኖች

ወገኖቼ ! ከናንተ ጥያቄ ሲመጣ አልሰማሁም አላየሁም ብየ ማለፍ ክህደት መስሎ ስለታየኝ፤ ከሞላ ጎደል አቅሜ በፈቀደልኝ መጠን የጠየቃችሁኝን

ለመመለስ "አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ አወጣ" በሚል ርእስ ያዘጋጀኋትን ጦማር በታላቅ ትህትና አቀረብኩላችሁ።

የጻድቃንና የሰማእታት አምላክ የጽድቁን መንገድ ያሳየን !